# የመጸው(ፎል)-ክረምት(ዊንተር) ክትባቶች

**እነዚህ ክትባቶች ለምን አስፈላጊ ናቸው?**
COVID-19፣ ኢንፍሉዌንዛ (ፍሉ) እና የመተንፈሻ አካል ኢንፌክስ አምጪ ቫይረስ (RSV) ክትባቶች ለከባድ በሽታ የሚኖረውን ተጋላጭነትን ይቀንሳሉ። ሶስቱንም ክትባቶች በአንድ ጊዜ መውሰድ ይችላሉ።

## ክትባት

## ክትባቱን ማግኘት ለማን ይመከራል?

## ኢንፍሉዌንዛ

4 የኢንፍሉዌንዛ ቫይረስ ዓይነቶች ላይ ያነጣጠረ ነው።

**6 ወር እና ከዚያ በላይ የሆነ ሁሉ** የእንቁላል አለርጂ ያለባቸው ሰዎችም ጭምር አንድ ዶዝ መከተብ አለበት።

**ከ8 አመት በታች የሆኑ ልጆች** የመጀመሪያው ወቅት ሁለት ዶዝ መውሰድ አለባቸው።

## COVID-19

የኦምሪከን ንዑስ አይነት የሆነ፣ XBB ኢላማ በማድረግ ክትባቱ ተሻሽሏል።

የተሻሻሉ የሞደርና (Moderna)፣ ፋይዘር (Pfizer) እና ኖቫ-ቫክስ (Novavax) ክትባቶች ይገኛሉ።

CDC **6 ወር እና ከዚያ በላይ የሆነ ሁሉም ሰው** ካለፈው ክትባት ወቅት ቢያንስ ከ2 ወራት በኋላ የተሻሻለ የCOVID-19 ክትባት እንዲከተብ ይመክራል።

- ያልተከተቡ አብዛኛዎቹ ሰዎች ወቅታዊ ክትባት እንዳገኙ ለመቆጠር አንድ ዶዝ Pfizer/Moderna ወይም ሁለት ዶዝ Novavax መከተብ ያስፈልጋቸዋል።
- ከ6 ወር እስከ 4 አመት የሆናቸው ህጻናት እስካሁን ያልተከተቡ ከሆኑ፣ ሁለት ወይም ሶስት ዶዝ የCOVID-19 ክትባት እንዲወስዱ ይመከራሉ።

## RSV[1]

የመተንፈሻ አካል ኢንፌክስ አምጪ ቫይረስ (RSV)። የመተንፈሻ አካል ኢንፌክስ አምጪ ቫይረስ (RSV) በህጻናት እና በእድሜ ባለጸጎች አዋቂዎች ላይ ከፍተና ኢንፌክሽን ያስከትልባቸዋል።

**ዕድሜያቸው 60 እና ከዚያ በላይ የሆኑ አዋቂዎች** የጤና እንክብካቤ አቅራቢቸውን/ፋርማሲስታቸውን ስለ የመተንፈሻ አካል ኢንፌክስ አምጪ ቫይረስ (RSV) ክትባት መጠየቅ አለባቸው።

**ነፍሰ ጡሮች** በመተንፈሻ አካል ኢንፌክስ አምጪ ቫይረስ (RSV) ወቅት በ32 እና 36 ሳምንታት መካከል አንድ ዶዝ መከተብ አለባቸው (ጨቅላው ህፃን ከተወለደ በኋላ ለወራት የሚቆይ የበሽታ መከላከያ ያገኛል)።

[1] ነፍሰ ጡር ሴት የRSV ክትባት ካልወሰደች፣ ህፃኑ አንድ ዶዝ የበሽታ መከላከያ ክትባት (RSV) ሞኖክሎናል አንቲቦዲ እንዲወስድ ይመከራል ። ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው እስከ 19 ወር የሚደርሱ ህጻናት/ታዳጊዎች አንድ ዶዝ እንዲወስዱ ይመከራል።

ALAMEDA COUNTY HEALTH CARE SERVICES AGENCY
PUBLIC HEALTH DEPARTMENT

ለበለጠ መረጃ፣
covid-19.acgov.org/vaccines
የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ
ወይም የ QR ኮዱን ስካን ያድርጉ፥

ከ"**የመጸው/ፎል 2023 ክትባቶች** " በሚል ርእስ በKatelyn Jetelina፣ MPH PHD እና Caitlin Rivers፣ MPH PHD *የአከባቢዎ ኤፒዲሚዮሎጂስት ከተዘጋጀው እና የCDPH በራሪ ወረቀት፥* https://eziz.org/assets/docs/IMM-1481.pdf የተወሰደ፥